# ዜና አመዝኮ

ቅጽ 8 ቁጥር 10 ታኅሣሥ 1995

**አ** የአደጋ

**መ** መከላከልና

**ዝ** ዝግጁነት

**ኮ** ኮሚሽን

## በዚህ ዕትም የውስጥ ገጾች

- በድርቅ ለተጎዱ ወገኖቻችን በታኅሣሥ ወር ውስጥ ከብር 11.4 ሚሊዮን በላይ ተለገሠ፤
- ለታኅሣሥ ወር ከ685 ሺህ ኩንታል በላይ የምግብ ዕርዳታ ተመደበ፤
- የድርቁን አደጋ ለመቋቋም በሚደረጉ ጥረቶች ላይ ያተኮረ ውይይት ተካሄደ፤
- የኮሚሽኑና በሥሩ የሚገኙ መ/ቤቶች ሠራተኞች በድርቅ ለተጎዱ ወገኖች ከብር 89 ሺህ በላይ ለገሱ፤
- በመሠረታዊ ሂሳብ አያያዝ ላይ ያተኮረ ስልጠና ተሰጠ፤

ዜና አመዝኮ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽንና ተጠሪዎቹ የሚያካሂዷቸውን የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት እንቅስቃሴዎችንና ሌሎች ተጓዳኝ ተግባራትን የሚዘግብ ወርሃዊ ልሣን ነው።

በአመዝኮ የሕዝብ ግንኙነት የተዘጋጀ

☎ 152383 ✉ 5686 ፋክስ 514788
152430

# ለታህሳስ ወር 685 ሺህ ኩንታል በላይ የምግብ ዕርዳታ ተመደበ

*• በጥር ወርም ከ900 ሺህ ኩንታል በላይ የምግብ ዕርዳታ ለማቅረብ ቅድመ ዝግጅት ተደርጓል።*

በበልግና በመኸር ዝናብ እጥረት ሳቢያ የተከሰተው ድርቅ ባስከተለው ተፅዕኖ ለምግብ እጥረት ለተጋለጡ ወገኖች በታህሳስ ወር በጠቅላላው 685 ሺህ 339 ኩንታል የምግብ እህል ዕርዳታ ተመድቧል። ከዚሁ ዕርዳታ ውስጥ 300 ሺህ 101 ኩንታል በአመዝኮ ፣ 385 ሺህ 238 ኩንታል ደግሞ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች አማካይነት ለክልሎች ተመድቦ በአብዛኛው ለተረጂዎች እንዲከፋፈል ተደርጓል።

ለክልሎች የሚመደበው የምግብ ዕርዳታ በየክልሎቹ እንደሚገኘው ችግር ስፋትና ክብደት በቅደም ተከተል ሲሆን ፣ በዚሁ መሠረት ለታህሳስ ወር ከተመደበው የምግብ ዕርዳታ ውስጥ ለኦሮሚያ 275 ሺህ 416 ኩንታል ፣ ለትግራይ 20 ሺህ 067 ኩንታል ፣ ለአማራ 88 ሺህ 968 ኩንታል ፣ ለደቡብ 69 ሺህ 293 ኩንታል ፣ ለአፋር 66 ሺህ 482 ኩንታል ፣ ለሶማሌ 54 ሺህ 041 ኩንታል ፣ ለድሬደዋ 6 ሺህ 700 ኩንታል ፣ ለሐረሪ 3 ሺህ 200 ኩንታል እና ለጋምቤላ ሺህ 72 ኩንታል ተመድቦ ተከፋፍሏል።

በጥር ወር ለሚያስፈልገው የዕርዳታ አቅርቦት ክልሎች ባቀረቡት ፍላጎት መሠረት በድርቁ ለተጎዱ ወገኖቻችንን አልሚ ምግብን ሳይጨምር ከ900 ሺህ ኩንታል በላይ የምግብ እህል ዕርዳታ ለማቅረብ በኮሚሽኑና በተባባሪዎቹ /መያድ/ አማካይነት ከወዲሁ አስፈላጊው ቅድመ ዝግጅት በመደረግ ላይ እንደሆነም ታውቋል።

መንግሥትና ተባባሪዎቹ ድርቁ በተከሰተባቸው ክልሎች የደረሰውን የውሃ እጥረት ለማቃለልና የተረጂ ወገኖችን ፣ የእንስሳትን የጤና ሁኔታ በመከታተልና ተገቢውን የህክምና ድጋፍ በመስጠት ባደረጉት የተቀናጀ ጥረት በድርቁ አደጋ የተጎዱ ወገኖችን ሕይወት ለመታደግ ተችሏል። በመሆኑም ኮሚሽኑና በረድዔት ተግባር የተሠማሩ ተባባሪዎቹና መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በእስካሁኑ እያደረጉ ባለው የተቀናጀ ጥረት የተረጂ ወገኖቻችን ሕይወት በመታደግ የድርቁን አደጋ ለመቋቋም እንደተቻለ ሁሉ እ.ኤ.አ በ2003 ዓ.ም በተመሳሳይ እንቅስቃሴ ችግሩን በጋራ በመከላከል የተከሰተውን አሳሳቢ ሁኔታ ለመቆጣጠር እንደሚቻል ይታመናል።

## የድርቁን አደጋ ለመቋቋም በሚደረጉ ጥረቶች ላይ ያተኮረ ውይይት ተካሄደ

የፌዴራል አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን የሥራ ኃላፊዎችና የክልል አመዝ ኮሚሽነሮች ለአራተኛ ጊዜ ከታህሳስ 8-9 ቀን 1995 ዓ.ም ባደረጉት ወርሃዊ ስብሰባ በድርቁ ተጠቂ የሆኑ የሀገሪቱ አካባቢዎችን ወቅታዊ ሁኔታ የገመገመና አደጋውን ለመቋቋም በሚደረጉ ጥረቶች ላይ ያተኮረ ውይይት አካሂዷል።

ብፌዴራል አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን ሲሞን መቻሉ በተመራውና ለሁለት ቀናት በቆየው በዚሁ ስብሰባ ላይ በየክልሎች ያሉ ወቅታዊና ተጨባጭ ሁኔታዎች እንዲሁም የተለየ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች በየክልሎች የአመዝ ኮሚሽነሮች ቀርበው ሰፋ ያለ ውይይት ተደርጎባቸዋል። ከድርቁ አደጋ ጋር በተያያዘ የተከናወኑ ተግባራትን በተመለከተ በምግብ እህል ዕርዳታ አቅርቦት ፣ ሥርጭትና ክፍፍል፣ በሎጂስቲክስ በውሃ አቅርቦት ረገድ የተከናወኑ ተግባራት ተገምግመው በጠንካራና ደካማ ጎኖች ላይ ሰፋ ያለ ውይይት በማካሄድ በቀጣይም ዕቅድ በተሟላ መልኩ ለመፈጸም የሚያስችሉ የመፍትሔ ሃሳቦችን አስቀምጧል፡፡

በሥሩ ያሉ የናዝሬት፣ ሻሸመኔ፣ ኮምቦልቻ፣ ድሬደዋ ቀሊ፣ ይትና የ ሬታ ኦርጋኒክ እህል ክምችት ጋዘን ሠራተኞች ሺ ብር ከ60 ሳንቲም፣ እያ ከላ ልና ዝግጅትት ፈንድ ራተኞች ደግሞ ሺህ 19 ብር ከ30 ሳንቲም ከደመወዛቸው ቀን ለገሳቸው ታ ቋል።

ኮሚሽኑና በሥሩ የሚተዳደሩት ጠባበቂያ ምግብ ክምችትና እደ ላከልና ዝግጅትት ፈንድ ስተዳደር ሠራተኞች ዕርዳታውን ለመለገስ በወሰኑበት ጋራ ስብሰባ ያ ባደረጉት ይይት ለቤቶቹ ከተቋቋሙበት ዓላማ አኳያ በድርቅ ተጎዱ ወ ናቻችን ርዳትና ደገፍ ዘወትር ተግባራቸው ሆኑን እ ልክተው ከጠቅላላ ፍላጎቱ አንፃር ዕርዳታው አነስተኛ ሊሆንም፣ ጎን በጠጠር ይደገፋል እንዲሉ ከእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ጥረት ጋር ተዳምሮ ዕርዳታው ወገኖቻችንን ሕይወት ለ ታደግ እስተዋጽኦ እንደሚኖረው ያ ቸው ተስፋ ገልጸዋል።

ሠራተኞቹ በዚሁ ጊዜ እንደገለጹት በመስከም ሆነ በቢሮ ደረጃ በየተሰማሩበት ራ ዘርፍ ቀን ከሌሊት ሳይሉ ያለተጨማሪ ክፍያ በበዓል ቀናት ጭምር ለውቀታቸውንና ጉልበታቸውን በማስተባበር ኮሚሽኑ የተጣለበትን ታላቅ ኃላፊነት በሚገባ እንዲወጣ በማስቻል ተረጅዎችን ለመደገፍ እየተደረገ ላለው ጥረት ስኬታማነት ከመቼውም ጊዜ በላቀ የኃላፊነት ስሜት ለመንቀሳቀስ ዝግጁ ሆናቸውን አረጋግጠዋል።

ለወደፊቱም ድርቁ ሁኔታ እስከሚለወጥ ድረስ በመስክና በቢሮ በተ ደቡበት ያ በለለት ተዕለት ሥራቸው ደጋውን ለመቋቋም በዕውቀታቸውና በጉልበታቸው ከሚያበረክቱት እስተዋ ያ ጎን አቅማቸው ፈቀደውን የገንዘብ ድጋፍ ለማድረግ ቃል ገብተዋል

# በመሠረታዊ የሂሳብ አያያዝ ላይ ያተኮረ ስልጠና ተሰጠ

በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን ሥር ካሉ የተለያዩ መምሪያዎችና አገልግሎቶች ለተውጣጡ ባለሙያዎች በመሠረታዊ የሂሳብ አያያዝ ላይ ግንዛቤ የሚያስጨብጥ የሙያ ማሻሻያ ስልጠና ተሰጠ።

የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን ከኢትዮጵያ ሥራ አመራር ማሠልጠኛ ኢንስቲትዩት ጋር በመተባበር ከታህሳስ 14 እስከ 22 ቀን 1995 ዓ.ም በተሰጠው በዚሁ ስልጠና ሰጣኞቹ በሂሳብ አያያዝ መርህ ፣ የሂሳብ አያያዝ ምንነት ፣ በቢዝነስ ትራንዛክሽን ፣ በባንክ ሂሳብ አሠራር ፣ የንብረት ቆጠራ እና በሌሎችም ርዕሶች ላይ ግንዛቤ እንዲያገኙ መደረጉ ተገልጿል።

በአመዝኮ የሥራ አመራርና ማሰልጠኛ አገልግሎት አስተባባሪነት በተሰጠው በዚህ ስልጠና ላይ የተሳተፉት ከንብረት አስተዳዳርና ትራንስፖርት ማስተባበሪያ መምሪያ፣ ከኦዲትና ኢንስፔክሽን አገልግሎት ፣ ከፋይናንስ አገልግሎት ፣ ከጨረታና ግዢ የተውጣጡ 25 ባለሙያዎች ናቸው።

ስልጠናውን ከወሰዱት መካከል አንዳንዶቹ እንደገለፁት የዚህ ዓይነቱ ስልጠና ለተሰማሩበት ሥራ በብቃትና በቅልጥፍና መከናወን በእጅጉ የሚያግዛቸው በመሆኑ በቀጣይም በተጠናከረ መልኩ እንዲካሄድ ጠይቀዋል። መሠል የሙያ ማሻሻያ ሥልጠናዎች በቀጣይነት ለሠራተኞች ለየሚሰጡበት እቅዶች መኖራቸውን ከሥራ አመራርና ማሠልጠኛ አገልግሎት ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።